# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ
(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር)
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

ቁ. 70 መስከረም 20 1972


## ኢማሌድህ ከህብረት ወደ ክስረት = ስንኩል ሁኔታና ያተረፋቸው ተግባር

**መግቢያ**

"ኢማሌድህ ከህብረት ወደ ውህደት...ኢማሌድህ የወዛደሩ ፓርቲ በቸኛ ጥንስስ ነው... ኢማሌድህ በዚህ ይውረድ... ኢማሌድህ ከዚያ ይውጣ..." ሲባልለን ከረመና አሁን ደግሞ የተባለው፣ የተጻፈውን የተለፈፈውንና የተፈከረውን ሁሉ እንዳልነበር ረስቶ ምድረ አድርባይና አድሃሪ ሁሉ "በውህደት ፓርቲ መመሥረት እንደማይቻል ተደርሶበታል... ለወዛደሩ ፓርቲ ሌላ ጥንስስ መኖሩ ተረጋግጧል...ኢማሌድህ የአድሃሪያን መታገሪያ ሆና ፈርሷል..." "በኮምኒስቶች፣ በኮምኒስቶች አንድነት ...ማዕከል ..." እያለ ያዙኝ ለቀቁኝ በማለት ላይ ይገኛል::

ድርስ ቢሆን? ባለፈው ቀጥራችን የፖለቲካ ክስረት ዝርዝር ድርጅታዊ ክስረትን እንደሚያስከትል የፀፍነውን ልብ ያለ ሰው የከሠረው ኢማሌድህ በዚህ መልክ ወደ ታሪክ ቱቢያ መጣያ መውረድ ሊያስገርመው አይችልም:: የቀኝ ሃይሎች ዛሬ የፀረ አብዮት የማያል ደረጃ አመቻቹታቸው "ኢማሌድህ ፈርሷል" ብለው አፍ አውጥተው ለማወጅ በቁ እንጂ ኢማሌድህ የሚባለው ነገር ካለቀለት፣ ውርደትን ተከናንቦ ወደ ታሪክ ትቢያ መጣያ ከወረደ ሰንበት ያለ ጉዳይ ነው:: ኢማሌድህ ያለቀለት ዛሬ አይደለም:: ኢማሌድህ ያበቃለት ራሱ የተመሠረተበትን የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች ህብረት የጋራ መግለጫንና መርሃ ግብር ረግጦ፣ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አንቀፅ በአንቀፅ ሽር የፀረ አብዮትንና የብሄራዊ ውርደትን ቁልቁለት ተያይዞ መንገድ የጀመረ ዕለት ነው ::

ኢማሌድህ ይዞት በነበረው የክስረት ጎዳና ቀጥሎ ወደ ውህደት ከሽንገርኩ ብሎ የወዛደር ፓርቲ ተመሠረተ ሲባል ኖር እንኳን የኢትዮጵያ አብዮታዊያን አፍ ግለፅ ነበር:: ይሽንን ከከሠረ "ህብረት" የፈለቀ ከሣራ "የወዛደር ፓርቲ" በምንም ዓይነት እንደማይቀበሉት ደጋግመው ያስታወቁት ጉዳይ ነበር :: በዚው በከሣራና በፀረ ወዛደር መሥመር ላይ ተመርኩዞ፣ በዚው በአድራጎ የፓርቲ መመሥረት ዜና የሚታጠውን የዘይድ ባሬው የወዛደር ፓርቲ የኢትዮጵያ አብዮታዊያን አይቀበሉትም::

የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ በየጊዜው ደሙን እየገበረ የመሠረታቸውን የአብዮት አለኝታ የሆኑ ድርጅቶችን በፀረ ዲሞክራሲ ሰገበለት አድ ተወርቶ እያሠረ፣ በተራ ሹም ሽር ምገሽር ሽራቸውን እያወጡ፣ ታጋይ ዲሞክራቶችንና ሃገር ወዳዶችን እየረሸኑ፣ እያሰረሸ ና በየእሥር ቤት እያጎሩ፣ በጠቅላላው በአብዮት ላይ እንደዘራው በይፋ ከመነሳታቸው በፊት ብዙ ለማድበስበስ ሞክረዋል:: የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ የዚህን ፀረ አብዮት ሂደት ጥንስስ ተመልክቶ ይህንን ለማጋለጥ ሲነሳና የቀኝ አድርባዮች ለአድሃሪው ቢሮክራሲ ፊታውራሪ በመሆን መሊሶንን ማጥቃት ሲጀምሩ ለመከዱ የሞከረት ይሽንኑ ነበር:: ለማሳመን የፈለጉት በተራማጆች ሠፈር ምንም ልዩነት እንደሌለና አንዳንድ ችግሮች ቢኖሩ መሠረታቸው መኢሶን የሚያሳየው "የቡድን ስሜት" "የሥልጣን ጥም" እንደሆነ ለማሳየት መውደቅ መነሣት

ይዘው ነበር::

ነገር ግን መኢሶን ለዲሞክራሲ ቢሮና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለአብዮታችን ሂደት እንደ ህይወት እስትንፋስ ያስፈልገዋል ሲል፣ የቀኝ አድርባዮች ደግሞ በይፋ ሽንጧቸውን ገትረው ለፀረ ዲሞክራሲ ሲሟገቱ፣ መኢሶን ለብሄረሰቦች እኩልነትና አንድነት ሲዋደቅ፣ የቀኝ አድርባዮች ደግሞ ከትምክህተኞች ጋር ቆመው ሲያራግቡ፣ መኢሶን ሃገራችን የማገም ሃያል መንግሥት ተቀፃሳ እንዳትሆን ሲታገልና ብሄራዊ ነፃነቷ መደፈሩን ሲቃወም፣ የቀኝ አድርባዮች ፊታውራሪዎች ደግሞ በሃገራችን የባዕድን ቀምጥ መንግሥት ለማቋቋም ሲያገበድዱ፣ መኢሶን ለሀቀኛ የወዛአደር ፓርቲና ለሀቀኛ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሲታገል፣ አድርባዮች በወዛአደሩ ጀርባ ራሳቸውን የ"ወዛአደር ፓርቲ" ብለው ሰይመው ባቋራጭ ለሥልጣን ሲቋምጡ፣ መኢሶን ህዝባዊ ድርጅቶች ያብቡ እያለ ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር ሲጋፈጥ፣ የቀኝ አድርባዮች በስንት ታጋይ ደም የተገነቡትን ህዝባዊ ድርጅቶች በተራ ሹም ሽር ምንሽርሽራቸውን ሲያወጧቸው፣ እጅ ተወርቸ እያሠሩ ለአድሃሪው ቢሮክራሲ ሲያስረክቧቸው፣...በቀኝ አድርባዮችና በመኢሶን ገንባር ቀደምነት በሚንቀሳቀሰው የአብዮት ሰፈር መሃከል ያሉት ልዩነቶች በፀረ አብዮትና በአብዮት መሃከል ያሉ ልዩነቶች መሆናቸው ይፋ እየሆነ ሄደ::

የቀኝ አድርባዮች የመኢሶንን "የቡድን ስሜት" ሬዘ ለመተውና ልዩነቶችን ለማመን ስለተገደዱ ብዙም ሳይቆዩ በድርጅታቸን፣ በዲሞክራቶችና በሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ላይ ለአድሃሪው ሰፈር ፊታውራሪ ሆነው በአመፅ ተሠማሩ:: ምንም እንኳን መኢሶንንና ሌሎች ሃቀኛ አብዮታዊያንን "ፈርጣጭ" "ተንሸራታች" እያሉ ለማወናበድ ቢሞክሩም ከአብዮቱ ሠፈር የፈረጠጡና የተንሸራተቱ ማን እንደሆኑ ለመለየት ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ምንም ጊዜ አላወሰደበትም:: ስለሆነም ከሚያየውና ከሚሰማው በየዕለቱም ከሚኖረው ሃቅ ተነስቶ በቀኝ አድርባዮች ፊታውራሪነት የሚካሄደውን አመፅ ተቋቋመ::

ከዚህም ወቅት አንስቶ የኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ፍጥነት አስመሳዩን እያጋለለና እያጋለጠ አርቃኑን እያስቀረው በመምጣቱ ዛሬ ወለል ብሉ በመጣው የቀኝ አድርባዮች ክህደት ያልቀረጠለት ኢትዮጵያዊ አይገኝም ብንል ስህተት አይሆንም:: በዚህ በኩል ባለፈው ቁጥራችን በኢትዮጵያ ምድር ስላለው ከፍተኛ የፖለቲካ ጥራት፣ የመኢሶን የፖለቲካ መሥመር ትክክለኛነት ከዕለት ዕለት እየተረጋገጠ ስለመሄዱ ጽፈን ነበር:: ካለፈው ቁጥራችን ወዲህ ይህ ጥሪት ሌላ ተጨማሪ "እምርታ" አገኝቷል:: ይኸውም የወዛአደሮች ፓርቲ ጥንስስ እየተባለ ይለፈፍለትና ይደነፋለት የነበረው ከሣራው ኢማሌድህ በቀኝ ሃይሎች ትዕዛዝ፣ በቀኝ አድርባይ "ድርጅቶች" አገባቢነት በይፋ እንዲፈርስ መደረጉ ነው:: በዚህ "ሂደት" በውስጡ አሉ እየተባሉ ይወሸከትላቸው የነበሩት ከሣራ "ድርጅቶችም" ያው በመንግሥት ትዕዛዝ ፈርሰዋል!

የኢማሌድህ ልሳን "የህብረት ድምፅ" ቁጥር 5 ለየካቲት ወር 1971ዓ.ም. ባወጣው ቁጥሩ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የውህደት ቲዎሪ እንደማይሰራ አረጋገጠ፣ ኢማሌድህ መፍረሱን ካረጋገጠ በኋላ ከእንግዲህ የወዛአደሩ ፓርቲ ጥንስስ ይህ ኢማሌድህ የተባለ ነገር ቁርቶ አንዱ "በአብዮታዊው" ደርግ የበላይነት የሚቋቋም የምልመላ ቢሮ እንደሆነ ገልጿል:: የኢማሌድህ ልሳን ነኝ የሚለው "ህብረት ድምፅ" ቁጥር 6ትም ይኸንኑ በማጠናከር ስለዚህ የምልመላ ቢሮ "ማዕከል" አተተናል:: በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ወዛደሮች ፓርቲ /ዛሬ ደግሞ፣ ሠርቶ አደር እንዲባል ተወስኗል!!?/ ከላይ በአዋጅ ለማቋቋም በተደረገው "ታሪካዊ ውሳኔ" መሠረት "ያገባኛል የምትል ሁሉ "ማመልከቻህን" እያስገባህ ተመለመል" ተብሏል:: ወደዚህ በአዋጅ ይቋቋማል ወደ ተባለው የዘይድ ባሬ ዓይነት ፓርቲ ለመግባት የመራኮቱንና የመስገብገቡን "ክብር" ለአትሳ አድርባዮችና ለለየላቸው አድሃሪዎች ትተን እኛ የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ስለዚህ አዲስ ሁኔታና ስለሚወድቅብን ታሪካዊ ሃላፊነት በጥሞና መወያየት ይኖርብናል::

በዚህ አዲስ ሁኔታ አንጻር የኢትዮጵያ ማርክሲስቶች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ተግባር ምንድን ነው? ይኸንን ባጭሩ ከመመለሳችን በፊት ኢማሌድህ ከህብረት ወደ ክስረት ተዋርዶ ዛሬ ወደ ታሪክ ትቢያ መጣያ የወረደበትን ሂደት ብንመለከት መልካም ነው::

## ክፍል አንድ: የኢማሌድህ የክስረት ጉዞ

ለመሆኑ ኢማሌድህ ማን ነበር? ኢማሌድህን በመፍረሻው ዋዜማ ላይ ለተመለከተው ሰው ይህ ህብረት በምኑ ላይ "ማርክሲስት ሌኒኒስት" የት ላይ "የድርጅቶች ህብረት" እንደሆነ የሚያጠያይቅበት የሙሉ ክስረት ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር ይታወሳል:: በመፍረሻው ዋዜማ ኢማሌድህ "አብዮታዊ ሰደድ" ይባል የነበረው ድርጅት መጠሪያ ብቻ አልነበረም:: በመፍረሻው ዋዜማ ኢማሌድህ በአብዮታዊ ሰደድ ውስጥ ነግሶ የነበረው የነሳገሠ አስፋው እልም ያለ ፀረ ዲሞክራሲና የሥልጣን ጥሙን ለማርካት ለሚያስፈልገው ድጋፍ ሲል የሃገራችንን ክብር ለባዕዳን ያስረከበውን ፀረ ኢትዮጵያ ፖለቲካ በፊት አውራሪነት የመራው ክሊክ መጫወቻ ድርጅት ሆኖ ነበር:: ዛሬ ኢማሌድህ ሲፈርስ ከአብዮቱ ሰፈር አንድም የተቃወመ ቃል አለመሰማቱ በዚህ "ህብረት" ጠቅላላ ክስረትና ከውስጡ ያሉትን አብዮታዊያን ሁሉ "አጥርቶ" የዚህ ክሊክ ሌላ መጠሪያ ስም ሆኖ በመቅረቱ እንደሆነ ግልፅ ነው:: ነገር ግን ኢማሌድህ በተመሠረተበት ወቅት ሊፈርስ ዋዜማ ላይ የነበረው ክሣራ ድርጅት አልነበረም:: እንዲያውም በየካቲት 1969 ዓ.ም. ላይና ከዚያም በኋላ ለተወሰነ ጊዜ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደወዘደረ ፓርቲ ጥንስስ ቆጥሮት ሲደግፈው ቆይቷል:: ይህ ህብረት ተጠናክሮ ወደ ውህደት እንዲሸጋገርና የኢትዮጵያ ወዝአደሮች ፓርቲ እንዲመሠረት ሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ትግል አካሂዷል:: ነገር ግን የኢትዮጵያ አብዮታዊያን "ከህብረት ወደ ውህደት" ብለው የታገሉት፣ ኢማሌድህ በተመሠረተበት እምነና የጋራ መርሃ ግብር ላይ ፀንቶ እስከቆ ድረስ ብቻ ነበር:: ከዚያ መድረክ ሲገሸራቱና የፀረ ሕዝቦች መጫወቻ አሻንጉሊት ሲሆን ይህንን ክሣራ ህብረት የኢትዮጵያ አብዮታዊያንና ጥቆኖች በሙሉ አክ እንትፍ ብለው ተፍተውት ነበር::

የኢማሌድህ የመመሥረቻ መድረክ ምን ነበር? ከዚህ መሥመርስ ለምንና እንዴት ተገሸራትቶ በሰፊው ህዝብ ለመተፋት በቃ? እነዚህን ጥያቄዎች ባጭሩ ለመመለስ እንሞክራለን::

### ሀ/ የኢማሌድህ አመሠራረት:

ተደጋግሞ እንደተነገረው የማንኛውም አብዮት መሠረታዊ ጥያቄ የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ ነው:: የኢትዮጵያ አብዮት ከፈነዳበት ወቅት አንስቶ በዚህ ወሳኝ ጥያቄ ላይ ከፍተኛ ትግል ተካሂዷል:: በዚህ ትግል ውስጥ በአጠቃላይ ሁለት ሠፈሮች ተፋጠው በፖለቲካ፣ በርዕዮተዓለም፣ በድርጅት፣ ከዚያም አልፎ በትጥቅ ደረጃ ተፋልመዋል:: አሁንም እየታገሉ ናቸው:: በዚህ በሥልጣን ጥያቄ ዙሪያ የተደረጉት ትግሎች በአንድ በኩል በህዝብ ስም ከህዝብ በፊት በአቋራጭ ሥልጣን ለመያዝ በሚቋምጡ በቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ ፊትአውራሪነት የሚንቀሳቀሰው የአድሃሪ ቢሮክራሲና የጠቅላላው የቀኝ ሃይሎች ህብረት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በማርክሲስቶች፣ በዲሞክራቶችና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ግንባር ቀደምነት የሚዋደቀው የሰፊው ህዝብ ሰፈር ነው::

ከዚህ አንፃር ሲታይ ቀደም ሲል "በገራ" አድርባዩ በኢህአፓ ፊትአውራሪነት አድሃሪው ቢሮክራሲና ጠቅላላው ፀረ ህዝብ ክፍል ያነሳው የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት ጥያቄ የዚህ ፀረ ህዝብ ሴራ የማይነጠል አካል እንደሆነ ዛሬ ማንም የማይክደው ሃቅ ነው:: በመኢሶን ግንባር ቀደምነት ዲሞክራቶችና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ባካሄዱት ተጋድሎ ይህ አቋራጭ ሙሉ በሙሉ ተጋልጦ ኢህአፓ ወደ ታሪክ ትቢያነት ወረደ:: ከዚህ ድል በመነሳት በሚያዝያ ወር 1968 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ይፋ ወጥቶ ለሥልጣን ጥያቄ ሊሰጠው የሚገባውን መልስ አበሠረ:: ይህ ፕሮግራም የኢትዮጵያ ህዝብ ለዲሞክራሲያዊ ሥልጣን የሚበቃበትን ትልም አሳየ:: የኢትዮጵያ ህዝብ ለሥልጣን የሚበቃው የቀኝ ሃይሎች በሚታገሉለት ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት ሳይሆን፣ ንዑስ ከበርቴው ከላይ በሚያሮጠው ፓርቲ አማካኝነት ባይሆን በነቃ በተደራጀና በታጠቀ የረጅም ጊዜ ትግል፣ በሃፋና የወዝአደር ፓርቲና በሌሎች ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎችና ድር

ጅቶች ተበብር በሚቋቋም ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርና ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት እንደሆነ ተረጋገጠ:: ይህን ዓላማና ተልዕኮ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ ከዳር እስከዳር ተቀደቀለት:: ከዚህም ወቅት አንስቶ በቀኝ ኃይሎችና በአብዮታዊያን መካከል የተካሄደው ትግል የዚህን ፕሮግራም ከሥራ ላይ ማዋል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚቃወሙ ኃይሎችና በዚህ ፕሮግራም አርማ ሥር ተሰልፈው በመጋዝ በሚዋደቁ ታጋይ የኢትዮጵያ ልጆች መካከል ነበር::

በኢትዮጵያ "ማርክሲስት ሌኒኒስት ነን" ይሉ የነበሩት አምስት ድርጅቶች ከዚህ ሃቅ በመነሣት በአብዮቱ ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወተውን የወዝአደር ፓርቲ ለመመሥረት ከዚያም አልፎ ለሕዝባዊ ግንባሩ አስፈላጊ የሆኑትን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎችና ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲፈጠሩና እንዲፋፋ ለማገዝ ከፍተኛ ተጋድሎ ሲያካሂዱ ቆይተው ነበር:: በዚህም ትግላቸው በተለይ ለኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች አንድነት ያደረጉት ትግል ፍሬ ሰጥቶ በየካቲት ወር 1969 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ወዝደር ፓርቲ ጥንስስ ይሆናል ተብሎ ተስፋ የተጣለበትን የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ሕብረት "ኢማሌድሕ" መሠረቱ:: ይህ ለጠቅላላው በኢትዮጵያ ተራማጆች በተለይ ደግሞ ለኢትዮጵያ ወዝአደሮች አንድ ትልቅ የድል ምዕራፍ ነበር:: ታላቅነቱም ሕብረቱ መመሥረቱ ብቻ ሳይሆን ስለወደፊቱ ሂደትና ስለወዝአደሩ ፓርቲ አመሠራረት ሁኔታ፣ ስለማርክሲስት ሌኒኒስቶች አጣዳፊ ተግባሮች ለአስመሳይና ለከሃዲ ንዑስ ከበርቴዎች በምንም አይነት በማያወላዳ ሁኔታ ገለጸ የሆነ አቋም መያዙ ነበር::

የኢትዮጵያን አብዮትና ብሔራዊ ክብር ለሥልጣን ጥማቸው ማርኪያና ለፍርፋሪ በመሸጥ ከሁለት ዓመት ወዲህ ሊያደበሰብሱትና ሊያወድሙት ሞከሩ እንጂ ኢማሌድሕ ገና ሲመሠረት ስለወዝአደሩ ፓርቲ አመሠራረት ጉዳይ ቁልጭ ያለ ትክክለኛ አቋም ነበረው:: በጊዜው የወጣውን መግለጫ የፈረሙት ድርጅቶች በዚህ ጉዳይ ላይ እንደሚከተለው ብለው ነበር::

".....ከነዚህ የተለያዩ ቡድኖች በምን ዘዴ የወዝአደሩ ፓርቲ ለመሠረት ይቻላል ለሚለው ጥያቄ የብዙ አገሮች አብዮታዊ ትግል ታሪክና የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በመመርመር ከተለያዩ የወዝአደር ፓርቲ አመሠራረት ዘዴዎች ፍቱንና ሳይንሳዊ የሆነው ዘዴ ልዩ ልዩ ማርክሳዊ ቡድኖች ኃይላቸውን አስተባብረው የትግል አንድነት መሥርተው በመካከላቸው በታክቲክና በስትራቴጂ ጥያቄዎች ላይ ሃቀኛ የሆነ የርዕዮተዓለም ትግል አካሄደው የሚዋሃዱበት ዘዴ መሆኑን እምነንበታል::" ካሉ በኋላ ለዚህ ሃቀኛ የርዕዮተዓለም ትግል አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር በስውር ታፍነው የሚሠሩት ተራማጅ ድርጅቶች ትግላቸውን በይፋ ለማካሄድ እንዲችሉ "ባስቸኳይ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እንዲታወጁ" የጋራ ትግል ለማድረግ ወስነው ነበር:: ይህ ሂደት በእርግጥ ሃቀኛ የሆነ የኢትዮጵያ ወዝአደሮች ፓርቲ ለመመሥረትና ወደ ሕዝባዊ ሥልጣን ለመጓዝ ቁልፍ ከሆኑት ጥያቄዎች አንዱ የሆነውና የወዝአደር ፓርቲ ጥያቄን በአብዮታዊ መንገድ የሚመልስ ሂደት ነበር::

ነገር ግን በዚው በትክክል እንደተቀመጠውና በጋራ መግለጫውም ላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ትግላቸው ለወዝአደሩ ፓርቲ ብቻ አልነበረም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንድ ፓርቲ ብቻውን ሥልጣን የሚይዝበት ሂደት ፀረ አብዮትን እንጂ አብዮትን አያመጣም:: በኢትዮጵያ ሁኔታ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ሥልጣን ሊረጋገጥ የሚችለው ከወዝአደሩ ሌላ በሃገሪቱ ያሉ ዲሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ኃይሎች በመስላቸው ተደራጅተው

ግንባር ሲፈጥሩ ብቻ በመሆኑ በመግለጫው ላይ ይህ ነጥብ በግልጽ እንዲገባ መኢሶን ባካሄደው ከፍተኛ ትግል የተነሣ "...... ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ለመመሥረት የሚያስችሉትን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲያችና ሰፋፊ ድርጅቶች ለማቋቋም እንዲችሉ ባስቸኳይ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ መታወጅ አለባቸው::" ለዚህም የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች ይኸንን ተግባር ከሥራ ለማዋልና ህያው የሆነ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ለማቋቋም እንዲችሉ በዚህ መግለጫ ውስጥ በወዝአደሩ፣ በአርሶአደሩ፣ በወጣቶች፣ በሴቶች፣ በቀበሌዎች አካባቢ ጠንካራና ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲያብቡ፣ ለዚህ እንቅፋት የሆነውን አድሃሪ ቢሮክራሲ እንዲጋለጥና እንዲደመሰስ ለመታገል ቃል ገቡ::

በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በተተለመው መሠረት አብዮቱን ከግቡ ለማድረስ አስፈላጊ ከሆኑት መሣሪያዎች አንዱ ሕዝባዊ አብዮታዊ ጦር መሆኑን በመገንዘብ "ይህንን ሕዝባዊ አብዮታዊ ጦር ከወዝአደሩ፣ ከአርሶአደሩ፣ ከሌሎች ተራማጅ ሃይሎችና አሁን ካለው መለዮ ለባሽ ለአብዮቱ ከሚቆመው ወገን ማቋቋም የሚቻልበት ሁኔታ አለ:: አሁን ያለው የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ በመደብ ምንጩ ከድሃው ገበሬ እንደመሆኑ መጠን ከውስጡ የሚገኙትን ፀረ አብዮት ሃይሎች ከማፅዳት ከሠራዊቱ ይበልጡን ወደ ሕዝቡ ለመሳብ የማርክሲስት ሌኒኒስቶች ተግባር መሆን አለበት:: የቆየው የፊውዳል ቡርዥዋው ቢሮክራሲ እንዳለ ለአብዮቱ መቆም እንደማይችል ተገንዝበው ይህ ቢሮክራሲ እንዲሠበር መታገል ይኖርባቸዋል::" በማለት ለኢማሌድህ አባል ድርጅቶች ግልፅ የሆነ የትግል መድረክ ተከፍቶላቸው ነበር::

እንግዲህ ኢማሌድህ ሲመሠረት የተቀረቀረበት የጠራ መሥመር ይኸ ነበር:: የቀኝ አድርባዮች የዚህን መድረክ አንቀፆች አንድ በአንድ እየሻሩ ወደፀረ አብዮት በመንሸራተታቸው ኢማሌድሃቸውም ከሰር ከሰፊው ሕዝብ ተተፍቶ ለዘረው ታሪካዊ ውርደት በቃ::

ለ/ <u>የኢማሌድህ የከሥረት ሂደት</u>፣ ኢማሌድህ ከፖለቲካ ከሥረት ጋር ድርጅታዊ ከሥረት ተደርበበት ዛሬ በአድሃሪያቸ ግፊት በቀላሉ ሊፈርስ የቻለው በዚህ ከሥረት የተነሣ አብዮታዊያንና ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አክ እንትፍ ብለው ስለተፉት እንደሆነ ግልፅ ነው:: ዛሬ የኢማሌድህ መፍረስ ሁለት ችግሮችን ያሳያል:: በመጀመሪያ የቀኝ አድርባዮች በፈታኙራሪነት ወገተው ባዳከሙት የአብዮቱ ሰፈር ላይ የቀኝ ሃይሎች ህብረት በጠቅላላው መጠናከራቸውን ያሳያል:: ሁለተኛ ደግሞ በዚህ በቀኝ ሃይሎች ህብረት ውስጥ የነለገሠ አስፋው ክሊክን በተለያዩ ምክንያቶችና በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚቃወሙት ሃይሎች ማየላቸውን ያሳያል::

የመጀመሪያውን ነጥብ እንውሰድ:: እንደሚታወቀው የኢትዮጵያን አብዮት ሂደት ለመግታት ብሎም ለመቀልበስ የቀኝ አድርባዮች፣ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትና አድሃሪው ቢሮክራሲ የጠነሰሱት የቀኝ ሃይሎች ህብረት አብዮቱን ማጥቃት የጀመረው ከዛሬ ሁለት ዓመት ቀደም ሲል ነው:: የሰፊው ሕዝብ ድምፅ ቁጥር 68 ላይ ስለዚህ አዲስ የቀኝ ሃይሎች ህብረት መጠንሰስና አስተዳደግ ባጭሩ ተንትነናል:: እዚህ እንመለስበትም:: የዚህን ህብረት እየተጠናከረ መምጣትን ጉዳይ ስንተነትን ጊዜ እስካላመቸው ድረስ አብዮቱን በአብዮት ስም ለመዋጋት ይገደዳል እንጂ የፀረ አብዮቱ እድገት ደረጃ እንደፈቀደለት ክህደቱን ሁሉ ከዕለት ዕለት ይፋ እያወጣው ይሄዳል ብለን ነበር:: ከዚያን ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ጉድ ያሳየን ጀምሯል! የቀኝ ሃይሎች ህብረት ክህደት በድፍረት ይፋ እየወጣ ነው::

......6

አድሃሪ ሃይሎች በተለይም ግንባር ቀደማቸው የሆነው አድሃሪው ቢሮክራሲ የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች "ከተገላቸን" እያሉ "ገና ጊዜው አልደረሰም" እያሉ ሲያሸፍበት የነበረውን የዲሞክራሲ ጥያቄ ዛሬ "ዲሞክራሲ ጊዜው ያለፈበት ጥያቄ ነው" ማለት አምጥተዋል:: ያ ሁሉ ደም ተገብሮበት በኢትዮጵያ ምድር የሰደደውን የአብዮታችን መመሪያ የሆነውን ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ሽረን ከሱ የበላይነት ያለው "የአዲስ አበባ ማኒፌስቶ እናውጣ" እያለ ሽርጉድ በማለት ላይ ነው:: የቀኝ አድርባይ ድርጅቶችም በትዕዛዝ መፍረሳቸውን ባስታወቁበት የህብረት ድምፅ ቁጥር 5 ላይ ስለዚህ መመሪያነት ባገቱም ሳያነሱ እንዲያውም የአብዮቱን መመሪያ በታህሣሥ "በአብዮታዊው" ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የታወጀው የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም መሆኑን "አበሰረውልናል":: በአጠቃላይ "አዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት" ብሎ ከሶሻሊዝም በፊት በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ማለፍ የሚሉት ነገር "የንዑስ ከበርቴ ሶሻሊዝም ነው" እየተባለ መለፈፍ ተጀምሯል::

ህዝባዊ ድርጅቶችን በሚመለከት በኩል የቀኝ አድርባዮች በኢትዮጵያ አብዮት አንገት ላይ የጠመጠሙት የቢሮክራሲ ማነቆ ድርጅቶችን ሁሉ ምንሽርሽራቸውን ካወጣ በኋላ አሁን ደግሞ እነዚህ ድርጅቶች የተቋቋሙባቸው አላማዎች እንደገና መታየትና መሻሻል አለባቸው እያለ ለሽራቸው በመሰናዳት ላይ ነው:: በመጋቢት ወር ላይ የኩሉኔል መንግሥትን የደቡብ ክፍለ ሃገራት ጉብኝት በማስመልከት የተካሄደው የኢኮኖሚና የባህል ዘመቻ መምሪያ ጉባኤ ላይ አድሃሪው ቢሮክራሲ በይፋ ከጠየቀው ከአላማዎች ሁሉ በላይ የሆነ "የአዲስ አበባ ማኒፌስቶ" ጋር ጨምሮ የ 1969 ዓ.ም.ን እነ ኢህአፖ "የባርነት አዋጅ" ብለው የታገሉትን የሠራተኞች ጉዳይ አዋጅ "እንዲሻሻል" የሠራተኛው ተወካዮች የሌሉበት ኮሚቴ ማቋቋሙ ... ወዘተ ለዚህ "የድፍረት ሂደት" ጠቋሚ ማስረጃ ነው:: ገና ደግሞ ብዙ እናያለን:: በዚህ ሂደት ላይ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የቀኝ መንገደኞች ፕሮግራም ተብሎ በይፋ የሚሻርበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም::

ለማንኛውም ዛሬ ኢማሌድህ እንደዚያ እንዳልተፈከረለት፣ እንደዚያ የአድሃሪው ቢሮክራሲ መንጋ ከሰፊው ሕዝብ ተደባልቆ ካንገት በላይ "ይደግ የመንደግ" እያለ እንዳ ሳስተጋባ ሁሉ ዛሬ እንዲፈርስ ቀደረጉ የዚህ ፀረ አብዮት ሂደት የማይነጠል አካል ነው ለማለት ይቻላል::

የትኛው ህዝባዊ ድርጅት፣ የትኛው የአብዮቱ ተቋም እየፋፋ እንደ ሄደ ኢማሌድህ ይፋፋል? ካለፈት ሁለት ዓመታት ወዲህ የትኛው የአብዮቱ መፈክር፣ የትኛው የአብዮቱ ሰነድ ተከበረና የኢማሌድህ መርሃ ገብርና መድረክ ይከበራል? የትኛውም ሊከበር አይችልም:: ባለፈት ሁለት ዓመታት ውስጥ በቀኝ ሃይሎች ህብረት እያየለ መምጣት የተነሣ በታጋይ ኢትዮጵያዊያን/ት ደም ተገንብተው ማበብ የጀመሩት ህዝባዊ ድርጅቶች በሙሉ ፈራርሰዋል፣ እንደ ህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ ቤት አይነቶቹ ተቋሞችም እንደዚሁ ፈራርሰዋል:: የዛሬው "ባለሳምንት" ደግሞ ኢማሌድህ ሆኗል:: ዛሬ የኢማሌድህ በይፋ መፍረስ በጠቀላላው የቀኝ ሃይሎችን ህብረት መጠናከርና በተለይ ደግሞ በዚህ ህብረት ውስጥ የቀኝ አድርባዮችን መዳከም ያሳያል ስንል ምን ማለታችን ነው? በቀኝ ሃይሎች ሕብረት ውስጥ በፊታውራሪነት የተሰለፈት የቀኝ አድርባይ ድርጅቶችና ከነርሱ በስተጀርባ ያለው የሕብረቱ አንቀሳቃሽ የሆነው አድሃሪ ኃይል ለጊዜው "ታክቲካዊ" ህብረት ፈጠሩ እንጂ የአላማቸው ርቀት የተለያየ ነበር:: የፊታውራሪዎቹ ከበርቴያች "ሕልም" የአብዮቱን ሂደት ባለበት ገትተው ሥልጣናቸውን ለማደላደል እንጂ ሂደቱን ጨርሰው ለመቀልበስ አልነበረም:: ከፊታውራሪዎቹ በስተጀርባ በቀኝ አድርባዮች በስተቀኝ ያለው ፀረ አብዮት ግን ምስኪኖችን አድርባዮች ለጊዜው የአብዮቱን ሂደት ለማዘግዘግ እና በቁጥጥር ሥር ለማዋል በመሣሪያነት ይጠቀምባቸዋል እንጂ የሱ ዓላማ አብዮቱን ከመገታትም አልፎ መቀልበስ እንደሆነ ግልጽ ነበር:: አሁንም ነው::

......7

የአብዮትን ሰፈር ድርጅቶችና ተቋሞች /የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት፣ ኢማሌድህ ... ወዘተ/ በማመልከት በኩል የአድርባዮች ዓላማ እነዚህን ድርጅቶች ከሃቀኛ አብዮታዊያን "አጽድተው" በቁጥጥራቸው ሥር ማዋልና በአብዮቱ ስም ፀረ ህዝብ ሥልጣናቸውን ማጠናከር ነበር:: አድሃሪያቹ ደግሞ እነዚህን ድርጅቶችና ተቋሞች ከነቆሙበት መድረክ አፈራርሰው ለማጥፋት ይታገላሉ:: እዚህ ላይ ግን ሁለቱ ሃይሎች የሚሄዱበት ርቀት የተለያየ ቢሆንም በዚህ ሂደት ላይ ባሉት የመጀመሪያዎቹ እርምጃዎች ይስማማሉ:: ሁለቱም እነዚህ ድርጅቶችና ተቋሞች እንዳይፋፋ ዲሞክራሲን ያፍናሉ:: ያሻጥራሉ፣ ሁለቱም እነዚህ ድርጅቶችና ተቋሞች ከመኢሶንና ከሌሎች ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች በ"ማጽዳት" ላይ ይስማማሉ::

በዚህ ሁኔታ ፖስኪኖቹ የቀኝ አድርባዮች ከሁሉ "ተወርዋሪ" በመምሰልና የመደባቸው ዘለዓለማዊ ምልክት በሆነው ድንፋታ እየተወጠረጠሩ ሕዝባዊ ድርጅቶችን ከአብዮታዊያን "ለማጽዳት" በፊትአውራሪነት ታገሉ:: በዚህ ትግል ከቁጥጥራቸው ሥር ሊያውሏቸው ያዳክሟቸውን፣ ከሰፊው ሕዝብ ያቀራረቧቸውን ሕዝባዊ የነበሩ ድርጅቶች አድሃሪው ቢሮክራሲ በቀላሉ አፈራረሳቸው:: ዛሬ እነዚህ ድርጅቶች በአሻጥር ጠውልገው፣ በፀረ ዲሞክራሲ ታፍነው፣ በአድርባዮች ቁጥጥር ሥር በመሆናቸው በሰፊው ሕዝብ ተተፍተው ስለሚገኙ አሉ ወይስ የሉም እያሉ የሚያወራርዱበት የጣረሞት ደረጃ ላይ ደርሰዋል::

በአብዮቱ ተቋሞችም በኩል ይኸው ነው:: የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትን አድርባይ ድርጅቶች በተለይ ደግሞ የአብዮታዊ ሰደድ ክሊክ በራሱ ቁጥጥር ሥር ለማድረግ ስቦ ከአብዮታዊያን ለ"ማጽዳት" ሞከረ:: አድሃሪያን ግን ይኸ ተቋም ከተመሠረተበት ወቅት አንስቶ ያለሙና ይታገሉ የነበረው ይኸንን ተቋም ጨርሶ ለማፍረስ ነበር:: ዛሬ ይኸንን ተቋም ከመኢሶን ለማጽዳት የተከፈተው ዘመቻ ሁለት ዓመት ቢሆነው በዚህ በኩል የምናየው ምንድን ነው? የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት "የኢትዮጵያ አብዮት አለኝታ ነው" እያለ ሰፊው ህዝብ ያለተዋደቀለትን ያህል፣ ያ ሁሉ ታጋይ ደሙን እየገበረ ትግሉን ያሳፋፋመውን ያህል በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ጨርሶ ተተፍቶ፣ ከታጋዮች ፀድቶ አድሃሪያች እንዳልነበር አድርገው አውድመውታል:: የኢማሌድህም ከሥረት የተከተለው ጉዳና ይኸው ነው::

የቀኝ አድርባይ ንዑስ ከበርቴያች "ህልም" ኢማሌድህን ከአብዮታዊያን "አፅድተው"፣ ሥፍር ቁጥር የሌለው ታጋይ ወዝአደር ረሽነውና አስረሽነው፣ በሺህ የሚቆጠር ታጋይ በየእሥር ቤቱ ወርውረው፣ የአንድ ትውልድ ትግል ያፈራቸውን ማሌያች ለማስጨፍጨፍ መሣሪያ ሆነው በቁጥጥራቸው ሥር ካደረጉት በኋላ ማርክሲስት ሌኒንስቶች ለመድሃኒት የማይገኙበት "የማርክሲስት ሌኒንስቶች ፓርቲ" ያለወዝአደሮች የወዝአደር ፓርቲ ለመመሥረትና ከዚህ ከኢማሌድሃቸው ጋደ ውህደት በተሸጋገረ ፓርቲያቸው አማካኝነት ሥልጣን ለመጨበጥ ነበር! ነገር ግን ይኸንን ዓላማ ሲከተሉ ባደከሙት አብዮት አንፃር እየተጠናከረ የመጣው የቀኝ ሰፈር ኢማሌድሃቸውን አፈራርሶ የነለገሠ አሰፋው ክሊክ ብቻውን ሥልጣን ለመጠቅለል የቋመጠበት ሂደት ውሃ ገባ! ይኸ የጠቆሳሰው የአድሃሪው ሰፈር መጠናከር ደግሞ አንዱ ተርጉም በቀኝ ሃይሎች ህብረት ውስጥ የለየላቸው ቀለባሽ ሃይሎች በቀኝ አድርባዮች ላይ የበላይነትን ተቀዳጁ ማለት ነው:: ይኸንን የሃይል ሚዛን ለውጥ በይበልጥ ጠጋ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል::

ከላይ እንዳልነው የኢማሌድህ መፍረስ በቀኝ ሃይሎች ህብረት ውስጥ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከልዩ ልዩ አቅጣጫዎች በአብዮታዊ ሰደድ ውስጥ የበላይነትን ይዞ የነበረውን የነለገሠ አሰፋውን ክሊክ የሚቃወሙ ሃይሎች ገፊት እንደሆነና የዚህን ክሊክ መዳከም

የሚያባይ ነገር ነው ብለናል:: ዞር ዞር ከማራው ኢማሌድህ የወዝአደር ፖርቲ ጥንስስ ከመሆን አከተመ ነበር:: ይህንን አብዮታዊያንም ፀረ ህዝቦችም ያውቁት ነበር:: ኢማሌድህ ይፍረስ በተባለበት ጊዜ ይህ በትር የተከነዘረው በተለይ በነለገሠ አስፋው ክሊክ ላይ ነው የምንለው ኢማሌድህ ከሁለት ዓመታት ወዲህ "እየፀነ እየፀነ ጨጎተ" የዚህ ክሊክ ሌላ መጠሪያ ስም ስለነበረ ነው:: የቀኝ አድርባዮች በአብዮታዊያን ላይ ዘምተው ከዚያ በኋላ ደግሞ እርስ በርስ በገጠሙት ግብግብ ተጓክመው የኢትዮጵያን አብዮት ገደል ይዘው ከመግባታቸው በፊት ስልጣንን ጠቅልለው ለመያዝ የቀየሱት ታክቲክ ነበራቸው:: ይህ ታክቲክ ምንድን ነበር? ዛሬ የዚህ ታክቲክ መከሸፍ ምን አዲስ ሁኔታ ፈጠረ?

ከኢማሌድህ መፈጠር በኋላ በአብዮታዊ ሰደድ እና ዛሬ በአዋጅ በፈረሱት በሌሎች ማርክሲስት ሌኒኒስት ነን ይሉ የነበሩ ድርጅቶች አድርባይ መሪዎች የተጠነሰሰው የሥልጣን ባይራጥ ሴራ ሁለት ምዕራፎች ነበሩት:: የመጀመሪያው ምዕራፍ ኢማሌድህን ከሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች አጽድቶ በአብዮታዊ ሰደድ ቁጥጥር ሥር ማዋልና ይህንን ከማርክሲስት ሌኒኒስት ጠርቶ "ማርክሲስት ሌኒኒስት" የሚባለ፣ ከድርጅቶች ጠርቶ " የድርጅቶች ሕብረት" የሚባል ቁፍ ነገር " አዋህደ" ወደ ወዝአደር ፖርቲነት መለወጥ ነበር:: ሁለተኛውና ከዚህ የሚከተለው ምዕራፍ ደግሞ በዚህ "የወዛደር ፖርቲ" አማካኝነት "ገዐስ ከበርቴ" " ወሳዋይ" ይባል የነበረውን ደርግ አፍርሶ ስልጣንን በአብዮታዊ ሰደድ ክሊክ እጅ መጠቅለል ነበር::

ይህንን ታክቲኩን የተገነዘበ ሰው ባለፉት ሁለት ዓመታት የአብዮታዊ ሰደድ ክሊክ ለምን ኢማሌድህን ሊጠቀምበት እንጂ ሊያፈርሰው እንዳለፈለገ ይገነዘባል:: ይህንን ታክቲኩን የተገነዘበ ሰው አብዮታዊ ሰደድና ሌሎች የቀኝ አድርባዮች የሚከተሉት ፀረ ወዝአደርና ፀረ ሕዝብ ፖለቲካ ይፋ እየወጣ ሲሄድ ስለወዝአደሩ ፖርቲ አጣዳፊነት፣ ስለኢማሉድህ ከሕብረት ወደ ውህደት መሸጋገር የአብዮታችን የሞት የሽረት ጥያቄ መሆን ወዘተ. የሚደረገው ቅስቀሳ ለምን እየጠመረ እንዳሄደ ይረዳል:: ይህ ሁሉ ድንፋታ ኢማሌድህን ወደ ወዝአደር ፖርቲ ለውጦ ስልጣን ለመጠቅለል የቀኝ አድርባዮች መሻሞጥ እንደነበር ገለጸ ነው:: የአብዮታዊ ሰደድ ክሊክ እና ሌሎች የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች መሪዎች ይህንን " ኢማሌድህን በቁጥጥር ሥር ማዋል" የሚለ ፖለቲካ ሲያባርሩ ለአንድ አመት ተኩል ያህል በአብዮቱ ሰፈር ፀረ ሕዝብ አመጽ አወረዱ:: ከኢማሌድህ ውስጥ መኢብንንና ኢጭአትን አባረሩ:: ይህ ጉዳይ "ተጠናቀቀ" የነሰደድ ወደ ወዝአደር ፖርቲነት መለወጥ እየተቃረበ ሲሄዱ እምና በሚያዝያ ወር " በህብረት ድምጽ" ጋዜጣቸው ላይ " ሰፊው ሕዝብ ... አስተማማኝ የወዝአደር ፖርቲ ይመሥረት ይላል .... ያሳአንዳቸ መታከት ኢማሌድህ ይጠናከር እያለ ያስተጋባል:: በአጠቃላይ ሰፊው ሕዝብ ተጨባጩ ሁኔታ በሚጠይቀው መሠረት በወዝአደሩ ፖርቲ ለመመራት ያለው ፍላጎትና የጋለ ስሜት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል::" ብለው ነበር::

የአብዮታዊ ሰደድ ወደ ውህደት የመሸጋገር መሻሞጥ ከዚህ ላይ አለቆም:: ተገሽ ቁጌ ተው ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተመርጠው ሕዝባዊ ድርጅቶችን በገነባር ቀደምነት እየመሩ የታመቁትን ሃይሎች ሁሉ እየለቀሙ የመረሸኑን እና በእሥር ቤት የማጉሩን ተግባር እንዳጠናቀቁ፣ በዚህም ሕዝባዊ ድርጅቶችን በቁጥጥራቸው ሥር ያደረጉ እንደመሰላቸው በሰኔ ወር 1970 "የሰፊው ሕዝብ የሥልጣን መሠረት የሆኑት ድርጅቶች ራሳቸውን ለኢማሌድህ አመራር አዘጋጅተው ኢማሌድህ አመራር ይስጠን ..." እያሉ በማመን ላይ መሆናቸውን አብዮታዊ ሰደድ ቁጥር 21 ላይ አበሰርለን ነበር!

ታዲያ እንደዚሁ መጣ፣ ደረሰ እየተባለ ሲሄድና አድርባዮች "የወዝአደር ፖርቲ" ብለው የዘያድ ባሬን ዓይነት ፖርቲ ለማዐጅ ሲሲናዱ በአካባቢያቸው ሌላ የሥልጣን ግብግብ ምዕራፍ ተከፈተ:: "በዚያው ሰሞን" ይለናል የሕብረት ድምጽ ቁጥር 5 " በዚያው ሰሞን በኢማሌድህ ውስጥ አንድ ያልተጠበቀ /?/ ሁኔታ ተከሰተ:: ይኸውም በአብዮታዊ ሰደድና በወዝአደር ሊግ መካከል የታየው ጩገበሰብ ቀራኒ ነው::"

ማንም እንደሚያውቀው ይህ ቅራኔ በነለገሠ አሰፋው ክሊክ፣ በአንድ በኩል፣ በራሱ በሰደድ ውስጥ ይገኝ በነበረ ዛሬ በታሠረና በተረሸኑ አባላትና በወዝ ሊግ በሌላ በኩል የፈነዳ ቅራኔ ነበር:: ጥሉ በዋና መልኩ የሥልጣን ግብግብ ነበር:: የፖለቲካ መሥመር ልዩነት ቢኖር ለሰፊው ህዝብ የተነገረው በይፋ ውይይት የተካሄደበት ነገር የለም:: አልነበረምም:: በጊዜው በይፋ የተገለፀውና በአብዮታዊ ሰደድም ሆነ በእነሱ "ተራማጅ" በተባለው የወዝአደር ሊግ አመራር እንደተገለፀው ከሆነ ጉዳዩ "የቁልፍ ቦታዎች" ንትርክ ነበር:: የአብዮታዊ ሰደድ ክስም የሚለው ይኸንኑ ነበር:: በዚህ በህብረት ድምፅ ቁጥር 5 ላይ "የወዝአደር ሊግ አድሃሪ አመራር አንዳንድ አባላቱን በአብዮታዊ ሰደድ ውስጥ አስርጎ በማስገባት ሁለቱን ድርጅቶች በአንድ ማዕከል ሊቆጣጠር መቀየሱ ነው::" ተብሏል:: እንግዲህ በሰደድ ውስጥ የነለገሠ አሰፋውን ክሊክ በሥልጣን የተጋፋ ሁሉ ለአድሃሪነቱ የማያወላዳ ማስረጃ ተገኘበት ካልተባለ በስተቀር ጥቅጥቅ የተነሳበት የፖለቲካ ልዩነት እስከዚህም ግልፅ አይደለም:: የሆነ ሆኖ በዚሁ በህብረት ድምፅ ውስጥ እንደተባለው ኢማሌድህ "ቀደም ሲል ያጋጠሙትን ችግሮች እንደተወጣ ሁሉ በመጨረሻም የተከሰተውን አሳሳቢ ቅራኔም ተወጥቷል::" ማለትም ኢማሌድህ በርግጥ በአብዮታዊ ሰደድ ውስጥ የነገሠው የነለገሠ አሰፋው ክሊክ ሌላ መጠሪያ ስም ሆነ:: በርግጥም እንግዲህ እንደዚሁ ክሊክ ቢሆን ኖሮ ኢማሌድህ ከህብረት ወደ ውህደት ለመሸጋገር ምንም እንቅፋት አልነበረበትም!

የአብዮታዊ ሰደድ ክሊክ ወደ ሥልጣን ጥቅለላ በተለመው ጊዜ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ለማከናወን ለአድሃሪያኑ ፊትአውራሪ በመሆን በአብዮታችንና በብሄራዊ ክብራችን ላይ ከፍተኛ ወንጀል ፈፀመ:: ይህ "የሥልጣን ባይራጥ" ዓላማው የጠየቀውን የማርክሲስት ሌኒኒስቶች፣ የዲሞክራቶችና የአገር ወዳዶች ደም አፈሰሰ:: ከ 20 ሺህ በላይ የሚቆጠሩ ተራማጅ ኢትዮጵያዊያንን በየእሥር ቤቱ ወረወረ:: የውስጥ ፀረ አብዮት ሃይሎችን ቡራኬ ለማግኘት የተውሉትን ግንባር ቀደም ሃይል ጨፈጨፈ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችን ምንሽርሽራቸውን አውጥቶ የተቋጠረውን ሁሉ በታተነ፣ የውጭ ሃይሎችን ድጋፍ ለመቃረም የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የወታደራዊ፣ የባህልና፣ የትምህርት ተቋሞች የባዕዳን ተቀጣሪ እንዲሆኑ፣ በኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታ ሳይሆን የውጭ ባለሥልጣኖች ቅምጥ መንግሥት ለማቋቋም ሽንጡን ይዞ ተሟገተ:: ይኸንን የተቃወመ ሃይል ሁሉ በተለይ በጦር ሃይላችን ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን ተራማጅና አገር ወዳድ መለዮ ለባሾች "በወዝአደራዊ አለም አቀፋዊነት" ስም ጨፈጨፈ:: የትምክህተኞችን ቡራኬ ለማግኘት በኢትዮጵያ ብሄረሰቦች መካከል እንደገና የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካን አስፋፋ:: ይኸንን ሁሉ አድርጎ በኢትዮጵያ አብዮትና ብሄራዊ ክብር ጣረሞት ላይ ተጠናክሮ የመጣ ሲመስለው "የወዝአደር ፓርቲ" የሚለውን የመንግሥት መሥሪያ ቤት አቋቁሞ ሥልጣን ለመጠቅለል ቋመጠ:: ይህ ታክቲኩ ስለከሸፈበት ሁኔታ ከመዘርዘራችን በፊት የዚህ ሥልጣን ጥቅለላ ጊዜ ሁለተኛ ምዕራፍ ምን እንደነበር እንመልከት::

የዚሁ "የሥልጣን ባይራጥ" ታክቲክ ሁለተኛ ምዕራፍ ባይራጥና በወዝአደሩ በስተጀርባ በተቋቋመው የወዝአደር ፓርቲ አማካኝነት "ንዑስ ከበርቴ ወላዋይ" ይባልለት የነበረውን ደርግ አፍርሶ ሥልጣንን መጠቅለል ነበር:: በዚህም ጥያቄ ላይ አብዮታዊ ሰደድ ቀደም ሲል ከተራማጆች ጋር ተደባልቆ ትክክለኛውን አቋም ይዞ ሲያስተጋባ መቆየቱ ይታወሳል:: ዛሬ በዚህ ጥያቄ ላይ አቋሙን መቶ ሰማንያ ዲግሪ ለመለወጥ ተገደ ምንም ዓይነት ሃፍረት ሳይሰማው ተቃራኒውን ይዞ እስከሚሟገት ድረስ ከአብዮታዊያን እኩል የጠራ አቋም ነበረው:: የንዑስ ከበርቴውን ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ታሪካዊ ሚና በመመልከት በኩል ደርግ የወላዋይ ንዑስ ከበርቴ መደብ የማይነጠል አካል እንደሆነና የኢትዮጵያን አብዮት በምንም ዓይነት ከግቡ ሊያደርስ የሚችል ሃይል አለመሆኑን አብዮታዊ ሰደድ ሙሉ በሙሉ ይቀበል ነበር::

"የወዝአደሩ ፓርቲ ተፈጥሮ አመራር የመጨበጡን ጥያቄ አንገብጋቢ ከሚያደርጉት መሠረታዊ የአብዮቱ ጥያቄዎች መሃል መነሳት ያለበት አብይ ጉዳይ የሰፊው ሕዝብ ሥልጣን የጨበጠው ጊ. ወ. አ. ደርግ ታሪካዊ ሚና ጉዳይ ነው:: ደርግ በደርግነቱ

....10

በሚወክለውም መደብ አንፃርና በአብዮታዊ ሂደት ተጀዱ ታሪካዊ ሚናው የሚመዘነው ከሥር በንቃት፣ በድርጅትና በትጥቅ እየዳበረ በተራማጆች ህብረት/ ማለትም ሰደድ ! — ሰሀድ —/ እየተጠራ ከሚመጣው ሕዝባዊ ሃይል አንፃር ነው:: የኢትዮጵያ አብዮት ከውስጥም ሆነ ከውጭ የወጠሩት ጠላቶቹ እያበጡ ሲመጡ ደርግ አመራር መስጠት በሚገባው ወቅት ሰፊውን ሕዝብ አንቀሳቅሶ ለወሳኝ ፊልሚያው ለሚያደርገው ትግል ውጤት ኢማሌድህ ተጠያቂ ይሆናል:: ይህንን ሃሳብ ለመጠቆም የተገደድነበት ዋናው ምክንያት ደርግ ባለው የመደብ ፀባይና ይዞት የፈለገውን ያህል ተራማጅ ቢሆን ለሰፊው ሕዝብ ንቃት፣ ድርጅት፣ ትጥቅ አመቺ ሁኔታን ከመፍጠር ለሃቀኛ ተራማጆች ትግል በሕዝባዊ ጉት አማካኝነት ድጋፍ ከመስጠት ሌላ እንዲሁም በጊዜያዊ መንግሥትነት የመንግሥት ሃላፊነትን ከመዐጣት ሌላ ስለወዝአደሩ ፓርቲ መፈጠር የሚኖረው ሚና የተለየ ሊሆን አይችልም" አ.ሰ. ቁ. 19 ታህሣሥ 1970::

ይኸው ፅሁፍ ዝቅ ብሎ "ከዛሬው ደርግ ባሻገር" ትግሉን ለመቀጠል የሚያስችል የወዝአደር ፓርቲ ለኢትዮጵያ አብዮት ሂደት እጅግ አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ያሳያል:: ይኸንን ፅሁፍ በረጅሙ የጠቀስነው ሆን ብለን ነው:: በዚህ ጥቅስ ውስጥ "የደጉ ጊዜ" አብዮታዊ ሰደድ ብቻ ሳይሆን የጠቅላላው የተራማጆቹም አቋም በመሆኑ ነው: ከዚህ ጥቅስ እንደሚታየው አንደኛ ደርግ በሚወክለው መደብ የተነሳ በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ በአመራር ሚናው የሚለረሰረሰበት ታሪካዊ ወቅት ይመጣል:: ይህ በሚመጣበት ሰዓት ተራማጆች ትግሉን "ከዛሬው ደርግ ባሻገር" አካሂደው አብዮትን ከግቡ ለማድረስ እንዲችሉ የወዝአደር ፓርቲ መሥርተው ለመራመድ መዘጋጀት አለባቸው:: ሁለተኛ እንደዚህ አይነቱ የታሪካዊ መለፈ ሰፈስ ወቅት ሲመጣ ለአብዮቱ አመራር የወዝአደሩ ፓርቲ ብቸኛ ጥንስስ የተባለው ኢማሌድህ ተጠያቂ ይሆናል:: ሶስተኛ ደርግ የፈለገውን ያህል ተራማጅ ቢሆን ንዑስ ከበርቴ በመሆኑ የወዝአደሩን ፓርቲ ለመፍጠር አይችልምና በዚህ በኩል ገብቼ አፈተፍታለሁ ቢል ተቀባይነት አይኖረውም የሚሉ ሃሳቦች ይገኛሉ::

ይኸ ሁሉ የአብዮታዊ ሰደድ አቋም ምንኛ አብዮታዊ ነበር! ታዲያ ምን ይሆናል! ይኸን ሁሉ የአብዮት ሂደት ተቀብሉ የነበረው ለሱ የሥልጣን ባቋራጭ መቋምጥ ያመቸው መስሉት ነበር:: ይኸንን ዓላማ ሲያባድድ የወዝአደር ፓርቲ ብሉ የሚሰይመውን የፀረ ሕዝብ ጉረና ሲገነባ እንኳን "የጦጥ" ተራማጆችን ቁርቶ በራሱ በሰደድ ውስጥ የነበሩትን ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች አሠረ፣ ረሸነ:: ጠቅላላውን ተራማጅ ሰፈር በፊትአውራሪነት አዳከመ:: ሰደድ ራሱ ከላይ የጠቀስነው የነለገሠ አሰፋው ክሊክ መጫወቻ ሆኖ ፈራረሰ:: ደርግን አፍርሶ ሥልጣን የሚይዘው በነለገሠ አሰፋው ጥንስስነት የሚቋቋመው "የወዝአደር ፓርቲ" ሳይሆን በራሱ "በአብዮታዊው ደርግ" በሚቋቋም በአድሃሪው ቢሮክራሲ ቁንጮነት በሚንቀሳቀስ ሌላ "ማዕከል" ነው ተባለ:: በአብዮታችንና በእናት አገራችን ብሄራዊ ክብር ጣረሞት ላይ በቆሙ ሃይሎች ህብረት ውስጥ የሚካሄደው የሥልጣን ግብግብና መራኮት አንዱ ዙር በነለገሠ አሰፋው መዳከም አከተመ:: ገና ብዙ እናያለን:: ዝቅ ብለን እንደምናሳየው ይኸንን ክሊክ የተዋጉት የለየላቸው አድሃሪያች ብቻ አይደሉም:: ከደርግ ከራሱ ውስጥ አንስቶ ይኸ ክሊክ ፀረ ዲሞክራሲን ለማንገሥ ባሳየው ፊትአውራሪነትና ብሄራዊ ክብራችንን ለመሸጥ ባሳየው ደላላነትና ገሀድ እየሆነ በመጣው ትምክህተኝነቱ የተነሣ የተቆጡ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶችም በዚህ ትግል ተካፍለዋል:: በተጨማሪ ደግሞ የክሊኩ ሥልጣን ተጋፊነትና ተፋናቃኝነት ያሳሰባቸው ክፍሎችም በዚህ ዘመቻ ተካፍለዋል:: ስለሆነም በነዚህ በተሰበጣጠሩ ሃይሎች መካከል ከነለገሠ አሰፋው ክሊክ ባሻገር ሌላ የትግል ዙር በቅርቡ እንደሚጠብቀን ለመተንበይ አያስቸግርም:: የተራማጆች ተግባር የሚታለመው ከዚህ አኳኋና የተወሳሰበ ሁኔታ በመነሳት ነው::

....11

<u>ክፍል ሁለት: አዲሱ ሁኔታና የተራማጆች ተግባር:</u>

የዛሬወን አያድርገውና አብዮታዊ ሰደድ እነመሊብንን ውሃ በልቷቸዋል፣ የቀረነው እና ብቻ ነን እያለ የደነፋበት ወቀት በዚህ በወዝአደሩ ፓርቲ አመሠራረት ጉዳይ እና "ቀኞች" ስለምናስተጋባው አቋም እንደሚከተለው ጽፍ ነበር::

"አብዛኛውን ጊዜ ቀኞች የሚናገሩትና የሚሠሩት፣ የሚጽፉትና ወደ ተግባር የሚተረጉሙት ሁሉ ለየቅሉ ነው:: በተለይም የወዝአደሩን ፓርቲ ጥያቄ በሚመለከተው ጉዳይ ደበስባሳና ውልጥልጥ ያለ አቋም መውሰድና በተለያዩ ጊዜያት በለዩ ለዩ ፅሁፎቻቸው እንደ እስስት የሚቀያየሩ መንደርደሪያዎች እንደነበሩቸው የቀኞችን ለባን የተከታተለ ሃቀኛ ተራማጅ ሁሉ በተከከለ ሊገነዘበው ይገባል::" አ.ሰ. ቁ17 ታህሣሥ 1971::

የና "ገራዎችስ"! ሁለት ዓመት ሙሉ "በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የወዝአደር ፓርቲ በድርጅቶች ውህደት ይፈጠራል::" እያሉ አንዳሳስተጋቡ ሁሉ ዛሬ ደግሞ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ይኸው የውህደት ቲዎሪ እንደማይሠራ ሲያበሥሩልን በህብረት ድምፃቸው ቁ.5 ላይ "...በውህደት ስም ድርጅቶችን እንዳሉ በማገጣጠምና በውክልና /ኮታ/ የወዝአደሩን ፓርቲ ለመፍጠር የማይቻል መሆኑን" አመልክተ "በማርክሲዝም ሌኒንዝም ርዕዮተዓለም የታጠቁትን ዕውነተኛ ታጋዮች ማቀሃድ" አስፈላጊ መሆኑን በዚያው ባሰለመዱን ድንፋታ አስታወቁን ::

ሁለት ዓመት "ኢማሌድህ አማራጭ የሌለው ብቸኛ የወዝአደሩ ፓርቲ ጥንስስ ነው" ሲባልና ሲደነፋ ተከረምና ዛሬ ደግሞ ይህ ጥንስስ ፈረሰ ሌላ መቋቋሙን "የህብረት ድምፅ" "ፓርቲውን ለመፍጠር <u>በቅድሚያ</u> በአብዮታዊ ችሎታቸውና አስተዋፅዖቸው፣/ሚሪት/፣ ከኢማሌድህ አባል ድርጅቶችና መመዘኛውን የሚያሟሉ ከተገኙ ከአባል ድርጅቶችም ውጭ የሚገኙበት ማዕከል መመሥረት" አስፈላጊ እንደሆነ በመግለጽ አበሰርልናል::/የህብረት ድምፅ ቁ.6 ስለዚሁ ጉዳይ የተረከለንን ሌላ ጊዜ እንመጣበታለን::/

በመሃሉ ደግሞ የወዝአደሩ ፓርቲ መፈጠር ጉዳይ ሲነሣ "አመቺ ሁኔታን ከመፍጠር አልፎ ሌላ ጉዳይ ውስጥ መፈትፈት የለበትም" ይባል የነበረው ንዑስ ከበርቴ ከየት መጣ ሳይባል "አብዮቱ ከተቀጣጠለበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁንም ቢሆን ማዕከል እንደነበረው፣ ይህም ማዕከል ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እንደሆነና እሱም አብዮታዊ መሆኑን..." ስምምነት የተደረሰ መሆኑ ተነገረ!

ባጭሩ ምን ለማለት ነው የሚፈለገው? በኢማሌድህ ውስጥ አብዮታዊ ሰደድ፣በአብዮታዊ ሰደድ ውስጥ የነገሠ አስፈሪው ክሊክ አይሉ ራሱን ወዝአደር ፓርቲ ሊለውጥና ደርግን አፍርሶ ሥልጣን ለመያዝ ቢሞክር ፓርቲም ብቻህን አትሆንም፣ ደርግንም ብቻህን አፍርሰህ አትተከም ተባለ ለማለት ነው:: በሁለቱም አንፃር የሰደድ የሥልጣን ሞኖፖል ህልም ቢያንስ ለጊዜው ውሃ ገባ ማለት ነው::

አብዮታዊ ሰደድ ስለወዝአደር ፓርቲ መመሥረት ጉዳይ እንዲህ እንዲህ አይነት "እንደ እስስት የሚቀያየር" "ውልጥልጥ" ያለ አቋም ለመውሰድ ያስገደደው ምንድን ነው? ራሱን ለማፍረስ "የተከማማው"ለምንድን ነው! ወዶ አይደለም ተገዶ ነው::

ከሁሉ በፊት በአብዮታዊ ሰደድ ውስጥ እያየለ የመጣው የነገሠ አስፈሪው ክሊክ ዛሬ በጠቅላላው በኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ደግሞ በማርክሲስቶች፣በዲሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ጠርሶ የተተፋ ክሊክ ነው:: ዋና ድካሙ ይህ መተፋቱ ነው:: በፊትአውራሪነት ያካሄደው ፀረ ህዝብ ትግል ለአብዮቱ ሠፈር መዳከም ለፀረ አብዮት ማየል ያደረገውን እርኩስ አስተዋፅኦ ዛሬ በመክፈል ላይ ነው::

ነገር ግን ዛሬ አብዮታዊ ሰደድን ያፈረሱት ኃይሎች የተከበጠሩ ሃይሎች እንደሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል:: የኢትዮጵያ ማርክሲስቶች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች በዚህ ክሊክ ላይ ባሳዩት ጥላቻ ታውረው አሁን የሃይል አሰላለፍ ከመመዘንና አደጋዎችን ከማጤን መቆጠብ የለባቸውም::

ዛሬ ይኸንን በህዝብ የተተፋ ክሊክ ተረባርበው ያፈራረሱት ሃይሎች ውስጥ ከሁሉ በፊት አለም ያሉ ፀረ አብዮት ኃይሎች አሉ:: እነዚህ ኃይሎች በተለይ ደግሞ አድሃሪው ቢሮ

....12

ከራሲ የአብዮታዊ ሰደድ ከሌሎችም ሁነ ሌሎችን ዛሬ በአዋጅ የፈረሱትን አድርባይ ድርጅቶች በፊትአውራሪነትና በሙሃሪያነት ከተጠቀሙባቸው በኋላ ጡጦ እንዳለቀ ሎሚ እንደሚጥሏቸው ደጋግመን "የተነበይ ነው" ነገር ነው:: ለአድሃሪው ቢሮክራሲ ዛሬ የነዚህ ገዉስ ከበርቴዎች ታሪካዊ ሚና አክትሟል:: ስለሆነም ጠረርን ሊጥሏቸው ይፈልጋል::ዛሬ አድርባይ ድርጅቶች ሁሉ በተለይ ደግሞ የነለገሠ አሰፋው ክሊክ እንዲፈርስ ያዘዘው ዋና ኃይል ይኸ አድሃሪ ቢሮክራሲ ነው::

አድሃሪው ቢሮክራሲ የነለገሠ አሰፋውን ክሊክ ለመደምሰስና በሱ በራሱ ቁጥጥር ሥር ፓርቲውን ለመመሥረት ሲነሣ እነሱን አፍርሶ ይበልጥ አገር ወዳድ ይሆናል፤እነሱን አፍርሶ ያነሰ ተፃክሀተኛ ይሆናል ማለት የለየለት የዋህነት ነው:: አድሃሪው ቢሮክራሲ በነለገሠ አሰፋው ክሊክ ላይ የተነሣው ይኸ ክሊክ ፀረ ዲሞክራሲ ስለሆነ ሳይሆን ስልጣኑን ለመጠቅለል ስለፈለገ ነው:: አድሃሪው ቢሮክራሲ የነለገሠን "የቀምጥ መንግሥት" ፓለቲካ ቢቃወምና በውጭ ፓለቲካው በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አገር የገባውን ሌላ ሃያል መንግሥት ቢፄረር፤ሃገራችንን የሃቀኛ ገለልተኛ ፓለቲካና የብሄራዊ ነፃነት መሥመር ለማስያዝ አይደለም:: እሱ ደግሞ የእናት አገራችንን ክብር ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ለመሸጥ ነው:: ባጥሩ በዚህ በኩል የአድሃሪው ቢሮክራሲ ማየል በምንም አይነት የኢትዮጵያን ዲሞክራቶችና አገር ወዳጆች የሚያዝናና ሁኔታ አያመጣም::

ነገር ግን የነለገሠ አሰፋውን ክሊክ ያፈረሰው ሃይል ውስጡ ሌሎችም ሃይሎች አሉ:: በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን/ት/ ለዲሞክራሲ፤የብሄራዊ ነፃነትና የብሄረሰቦች እኩልነት ቆመው፤ ይህ ክሊክ የተከተለውን የጭፍጨፋ፤የፀረ ዲሞክራሲ፤ የፀረ ኢትዮጵያ ክብር፤ የፀረ ወዝአደር፤ፀረ ወጣት፤የፀረ ምሁር፤የፀረ ጭቁን ብሔረሰቦች ፓለቲካ በመቃወም የታገሉ ዲሞክራቶችና አገር ወዳጆች አሉ:: እነዚህ ኃይሎች ከደርግ ከራሱ ውስጥ አንስቶ በሌሎችም የሥልጣን እርከኖች፤ በተረፈ ሕዝባዊ ድርጅቶች ወዘተ. ቢገኙም አጅግ እየተዳከሙ ስለመጡ የረባ ቅንብር የሌላቸው ሃይሎች ናቸው:: ምንም እንኳን ዛሬ በሃገሪቱ በሰፈነው ፀረ ዲሞክራሲ ጨለማ ያልተቀጡ፤ በሃገራችን ክብር መደፈር ያልበገነ፤ በነዚያ ሁሉ ታጋይ ደም አበቦ የነበረው አብዮታችን መቀልበስ ያሳረረ ሃቀኛ ኢትዮጵያዊ ባይኖርም እነዚህ ዲሞክራቶችና አገር ወዳጆች አሁን ባሉበት ሁኔታ ይህንን ሁሉ ሃይል አስተባብረው ፀረ አብዮትን ለመቋቋም ገና አጅግ እንደሚያስቸግራቸው ገለጸ ነው::

ከዚህ የተወሳሰበ ሁኔታ በመነሳት መኢሶን ለኢትዮጵያ ተራማጆች የሚጠቅመው ነገር ምንድን ነው?

1ኛ/ ይህ የተፈጠረው አዲስ ሁኔታ ባለፈው የሰህድ ቁጥር ያደረግነውን "የትግል አንድነት ጥሪ" ይበልጥ አጣዳፊ አደረገው እንጂ በምንም አይነት አይለውጠውም:: ስለሆነም መኢሶን በሰፊው ህዝብ ድምፅ ቁጥር 69 ላይ ለኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች፤ ዲሞክራቶችና አገር ወዳጆች ያደረገላቸውን ጥሪ ያድሳላቸዋል::

2ኛ/ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ከከሃዲው ኢማሌድህ ይፈለጋል ተብሎ የነበረውን የዘይድ ባሪን አይነትን ፀረ ወዝአደር ፓርቲ እንደማይቀበሉት አስታውቀው ነበር:: በዚያው በከሃዲ ፖለቲካ ላይ፤ በአድሃሪው ቢሮክራሲ ቁጥጥር ሥራ በአዋጅ ይፈጠራል የተባለውንና ከአዲሱ ማዕከል ይፈለጋል የተባለውን "የወዝአደር ፓርቲ" አይቀበሉትም:: ሌላ "የክርስትና ስም" ሰጡት አሰሰጡት መሠረታዊውን ነገርም አይለውጠውም:: ከዚህም በመነሣት ለሃቀኛ የወዝአደሮች ፓርቲ ከዚህ መንግሥት የምልመላ ቢሮ ውጭ የሚያካሂዱትን ትግል ያለአንዳች ማወላወል ይቀጥላሉ::

...13

3ኛ/ በአድሃሪው ቢሮክራሲ ትዕዛዝ፣ ታሪክ በተፋቸው የአድርባይ ድርጅቶች መሪዎች አገበጋድነት እንዲፈርሱ በተከየነባቸው በአብዮታዊ ሰደድ፣ በወዝ ሊግ፣ በማሌሪድ ውስጥ የሚገኙ ሃቀኛ አብዮታዊያን ይህንን ትዕዛዝ እንዳይቀበሉ፣ በአዋጅ እንዳልተቋቋሙ ሁሉ በአዋጅ የማይፈርሱ መሆናቸውን አበሰረው፣ ካለፈው ኪሣራ አስፈላጊውን ትምህርት ቀስመው ለኢትዮጵያ ወዝአደሮች ፖርቲ መፈጠር የሚካሄትን ትግል ከሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ጋር ለማስተባበር እንዲገፉበት መሊብን ጥሪ ያደርግላቸዋል::

4ኛ/ በዚህ በተወሳሰበ ሁኔታ ውስጥ የነለገሠ አሰፋው ክሊክ ለአድሃሪያን ፊትአውራሪ ሆኖ በተጫወተው አሳፋሪ ሚና በመታወር ተራማጆች አሁኑ ሁኔታ የሚፈጥረውን አደጋ ከማጤን እንዳይቆጠቡ፣ በያለበት የህቡዕ አሠራር ስልታቸውን እንዲያቀናብሩና የህቡዕ መዋቅሮችን አጠናክረው እንዲሬመዱ ጥሪ ያደርግላቸዋል::

5ኛ/ በከሣራው ኢማሌድህ መፍረስ ውስጥ የነለገሠ አሰፋው ክሊክ ፀረ ዲሞክራሲና ፀረ አብዮታዊያን ፖለቲካ በመቃወም ተነሳስተው ሚና የተጫወቱ ማርክሲስቶች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ሁሉ በነሱና በለየላቸው አድሃሪያች መካከል ያሉት ልዩነቶች እየተጧጧፉ እንደሚመጡ በመገንዘብ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መድረክ ላይ ከሌሎች ተራማጆችና ከሰፊው ሕዝብ ጋር የትግል አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ መሊብን ጥሪ ያደርግላቸዋል::

============/============

— ይቀጥላል —